# ክቡር ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ምን እያስተማሩን ነው?

«በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደሆነች እወቁ በእርሳም ላይ ሂዱ » ኤር 6፤16

ከታዬ ብርሃኑ

በቅርቡ የተከበሩት ፕሮፌሰር ጌታቸው ሃይሌ በኢትዮ ሚዲያ ላይ ባወጡዋቸው ሁለት ፅሁፎች ላይ ሊያስተላለፉት የሞከሩት መልእክቶች ደረጃቸውን ያልጠበቀ፣ ስተው የሚያስቱ፣እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ፤ወቅቱን ያላገናዘቡ፣የማያንጹና ከፋፋይ ሆነው ስላገኝኋቸው ምንም ታናሽ ብሆንም እኔም የቤተክርስቲያኔና የሀገሬ ጉዳይ ያገባኛል በሚል ታላቁንና አንጋፋውን ሊቅ በዚህ ጽሁፌ መጠይቅና አስተያየት ማቅረብ ግድ አለኝ።

ወቅቱ የኢትዮጵያ ኦርዶቶዶክስ ቤተክርስቲያን በታሪኳ ገጥሟት በማያዋቅበት ሁኔታ በሀገር በቀል ጠላቶች በቅኝ አገዛዝ ስር ወድቃ በህይለኛ ማዕበል ፈተና ዕየተናወጠች የምትገኝበት ነው። እንደ ፋሽስቱ ኢጣሊያ አጀንዳ ኢትዮጵያዊነትን ለመዋጋት የኦርቶዶክስንና የአማራ አከርካሪ መምታት በሚል በደበቢት በረሃ አጀንዳ ቀርጾ አዲስ አበባ በገቡት የህወአት አባላት በአባይ ጸሀይና በአቦይ ስብሐት የሚዘወር «ሲኖዶስ» በሀገር ውስጥ ይገኛል። የአዲስ አበባው ሲኖዶስ ላለፉት 20 ዓመታት በሕገ ወጥ ፓትርያርክ ሲመራ ቆይቶ ዳግመኛ ፓትርያርክ በህይወት እያለ ቀኖና በጣሰ መንገድ ሌላ ህገ ወጥ ፓትርያርክ ለመምረጥ እየተዘጋጀ ነው። የሕወአት መራሹ መንግስት በፈጠረው የቀኖና ቀውስ ምክንያት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የቀኖና መከፋፈል ደርሶባታል። እነዚህም
፩፦ ህጋዊውን ፓትርያርክ የሚሰበስቡትን የጳጳሳት ጉባኤ (ሲኖዶስ) የሚቀበል፣
፪፦ህገ ወጡን ፓትርያርክ የሚሰብስቡትን የጳጳሳት ጉባኤ (ሲኖዶስ) የሚቀበልና
፫፦ ራሱን ገለልተኛ ብሎ የመደበው ነው። ገለልተኛው ቡድን የሚያራምደው አቋም ሲኖዶስ (የጳጳሳት ስብሰባ) በአገር ውስጥ ብቻ ነው የሚካሄደው፤ በስደት ላይ ሆኖ አይቻልም ስለዚህ ህጋዊው ፓትርያርክ በስደት የሚሰብስቡትን ጉባኤ አንቀበልም ይላል። በሌላ በኩል ደግሞ አቡነ ጳውሎስ ህገ ወጥ ናቸው አንቀበላቸውም ግን በሀገር ውስጥ የሚስበብስቡትን የጳጳሳት ጉባኤ እንቀበላለን የሚል ነው። በሌላ አነጋገር አቶ መለስን አንቀበልም ግን ፓርላማውንና ካቢኔውን እንቀበላለን የሚል ብሂል መሆኑ ነው።

በመሆኑም ወቅቱ ሀገራችንና ቤተክርስቲያችን ላይ በትግራይ ነፃ አውጪ ድርጅት አማካኝነት የታጋረጠውን ችግር ለመቅረፍ አንድ ሆኖ መታገልን ከምን ገዜ በላይ ይጠይቃል። በተለይም የአቡነ ጳውሎስን እልፈተ ሕይወት ተከትሎ የፈረሰውን ቀኖና እንዲጠገን የተፈጠረውን መልካም አጋጣሚ ገዢው መንግስት ያለ ሃፍረት በግላጭ በረጅም እጁ ሲያጨናግፍ ስለተስዋለ፤ በመላው ዓለም የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያንን አስቆጥቶዋል እንዲያውም ራሳችውን በገለልትኝነት የመደቡ ወገኖችም የቀድሞ ውሳኔያቸውን ፈትሸውና ቀይረው የህጋዊውን ቅዱስ ፓትርያርክ አመራር ከሚቀበሉ አብያተ ክርስቲያናት ጋር በሕብረት ሆነው ጠላት ዲያቡሎስን ለመታገል የውሳኔ ሃሳብ በማንሸራሸር ላይ እያሉ፤ ይህንን አይነት ቅዱስ ሃሳብ መጋራት ያልመረጡት እንዱሁም ህጋዊው ሲኖዶስ በሎስ አንጀለስ አስቸካይ ስብሰባ ላይ ያቀረበውን የአብረን እንስራን ጥሪ ለማኮላሸት የፈጠኑት ታላቁ ምሁር በመግቢያ ጽሁፋቸው ላይ ቅዱስ ገብርኤል በመልእክት ነገድ መለያየትና ሁከት እንዳይፈጠር የተናገረውን በመጥቅስ ባለንበት እንጽና አሉ። እንግዲህ በቀኖና ጥሰት ምክንያት ለሶስት የተከፈሉትን (ህጋዊው፣ህገወጡና ገለልተኛው )አብያተ ክርስቲያናት በዛው ፅኑ የሚል ከፋፋይ መልዕክት ነው። ይሄው መልዕክት ከራሱ ጋር በዛው አረፍተ ነገር ላይ ለሀገራችንንና ለቤተክርስቲያናችን ነጻነት በአንድነት እንሥራ ብሎ ከራሱ ጋራ ይጋጫል። ፕሮፌሰር! በማንና በምን ላይ ቆሞ አንድነቱ የሚፈጠረው? እንደኔ አንድ አሳብና ልብ ሆኖ አንድ ራስ ይዞ መታገል በራሱ የድል ዋዜማ ይመስለኛል።

በአንድ አካል ሁለት ራስ በሚለው ንዑስ ርዕሳቸው ላይ ታላቁ ምሁር ሁለት ፓትርያርኮች አንዱ አሜሪካ ሌላው ኢትዮጵያ ሆነው እኔን ተከተሉ ስላሉን ግራ ተጋባን ይሉንና እኛን የክርስቶስ ምእመናንን የቅዱስ ጳውሎስን መልእክት ጠቅሰው ሲያስተምሩን የጳውሎስ ወይም የአጵሎስ ነን እንዳንል በተለይም በውዝግብ ውስጥ በደጋፊነትና በወገንተኝነት ገብተን ለውዝግቡ ህይወት እንዳንሰጥ ይመክሩናል። ሆኖም በአንድ ዘመን አንድ ቤተክርስቲያን ሁለት ፓትርያርክ እንደማይኖራት ያስረግጡና አንዱን መከተል አለብን ብለው እንደገና ይህን አንቀጽ ያጋጩታል።የተከበሩ ፕሮፌሰር አንድ ምእመን እውነትን ፈልጎ ቀናውንና መልካሚቱን መንገድ ተከትሎ ከእውነት ጋር መወገን ክርስቲያናዊነት አይመስልዎትም? በህጋዊነትና በህገወጥነት፤በእውነትና በሀሰት በተፈጠረው ውዝግብ ህይወት ላለመስጠት መወሰን

ማለትየገለልተኝነትን ጎዳናናን፣ አቀም የለሽነትንና  ቅዱስ መጽሃፍ የሚጸየፈውን ለብ ያለ ሕይወትን ህይወት መምረጥ ማለት ነው። በራድ ወይም ትኩስ ያልሆነ ግን ለብ ያለ ህይወት መልካም እንዳልሆነ ራእይ 3፤16 ያስገነዝበናል። በአንጻሩ እንደ ህወአት አይነቱ አምባገነን ቡድን ገለልተኛነት እንደ አማራጭ አጀንዳ በካድሬዎቹ አማካይነት ያስፋፋል ይሄም ባትደግፉንም አትቃወሙን ነው ። በሌላ መንገድ ወያኔን መደገፍ ነው።

አንድ ፓትርያርክ መከተል እንዳለብንም በዙሁ አንቀጽ ላይ ይመክሩናል። ፕሮፌሰር - አንድን ህጋዊ ፓትርያርክ መከተል ምን ማለት ነው? የሚሰብስቡትን የጳጳሳት ጉባኤ እውቅና አለመስጠት አልፎም የሚያስተላልፉትን ውሳኔ  መቃወም እንዲያውም ምእመኑ በተግባር እንዳያውለው ፈጥኖ ማኮላሸት ይሆን? እባክዎ ያብራሩት
የችግራችን መንሥኤ በሚለው ርእሳቸው ላይ  ወያኔ የቤተክርስቲያንን ቀኖና በመጣስ  ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን በግፍ ከመንበራቸው ላይ እንደተገፉ ያምናሉ። ሆኖም ከመሰደድ ይልቅ እዛው ሆነው ቢሞቱ ለቤተክርስቲያን ክብር እንደነበር በመቆጨት ይነግሩናል። ፕሮፌሰር በዚህ አሳብ ብቻዎትን አይደሉም። የወያኔ ቡድን ርዕዮተ ዓለም አባት የሆኑት «አቦይ»ስብሐትም የዕርሶን ሃሳብ ይጋራሉ። በቅርቡ ሀገር ውስጥ በሚታተም ላይፍ በሚባል ጋዜጣ በሰጡት ቃለመጠይቅ ላይ ፓትርያርኩ ምንም እንካን ብንገፋቸውም መሞት እንደነበራቸው ቁጭታቸውን ግልጽ አርገዋል። «አቦይ» ስብሐት ዛሬ ላይ ሆነው በፓትርያርኩ ስደት የሚቆጩት ብጹዓን አባቶች ተሰደው እንደ አህያ ከመጮህ ሌላ እንዲህ አይነት ተዓምር ይሰራሉ ብለው አላሰቡም ነበር። ወያኔዎች እኔና እርሶ እርስ በርሳችን እንደምንባባለው ጎንደር፣ ጎጃምና ሸዋ ብለው ሳይሆን የሚያዩን አንድ ላይ በአህያ ተርታ ነው የሚያስቀመጡን።

ክቡርነትዎ! ስደትን እንደመስዋእትነት ያለመቀበል እምነትዎን ባልጋፋም፤ እግዚሔብሔር የቅዱስ ፓትርያርኩን ስደት ባርኮ በሚመሩት ቅዱስ ሲኖዶስ አማካኝነት በዓለም ዙሪያ በስደት የሚገኘውን ኢትዮጵያዊ ሕዝብ አሰባስበው መጠነ ሰፊ የሆነ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። ለማስታመስ ያህል  መሠሪዎቹ ወያኔዎች እንደ ደርግ በአዋጅ የፍየል ወጠጤን አዘፍነው ሳይሆን የሚገሉት በመኪና አደጋ በማስመሰል አልያም የተፈጥሮ ሞት እንዲመስል የመርዝ መርፌ በመውጋት አልባሌ አማማት እንደሚገሉ አይርሱ።

መፍትሔ በሚለው ንኡስ ርእሳቸው ላይ ሕጋዊ ሲኖዶስ ትኩረቱን ቅዱስ ፓትርያርኩን ከመንበራቸው እመመለስ ላይ ካረገ ዓላማውን የስልጣን ሽኩቻ ያስመስልበታል ብለው ይሰጋሉ።መንፈሳዊ እንቅስቃሴን  በዓለማዊ መነጽር ካዩት ሊመስል ይችላል። ግንኮ እንደርሶ ዓይነት ምሁር የህጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥረት የፈረሰ ቀኖና የመጠገንና የማስተካከል ትግልእንደሆነ  ጠንቅቆ የሚያውቅ የቤተክርስቲያን ልጅ የተባ ብእሮን ተጠቀመው ማሳወቅ ግድ ይሎታል።

ሲኖዶስ በሚለው ንዑስ አንቀጽ ላይ በሚያሳዝን ሁኔታ ኢትዮጲያውያንን ስደተኞች የፖሎቲካ፣የኢኮኖሚና የኃይማኖት ስደተኛ በማለት ይከፋፍሉቸዋል። አንድ ሰው በሀገሩ ላይ ተምሮ፤ሰርቶና፣ነግዶ መበልጸግ የመጀመሪያው ምርጫው ነው። ሆኖም ገዢው መንግስት  የሚራምደው ፖሎቲካ ብልሹ ስለሆነ ኢትዮጵያውያን በዓለም ዙሪያ ተበተኑ። በአጠቃካይ የህዝባችን ስደት ዋናው ምክንያት የህወዓት መርዘኛ ፖሎቲካ ውጤት ነው። ህጋዊ ፓትርያርክ መከተል አለብን ብለው ቀደም ባለው አንቀጽ ያስተማሩን ፕሮፌሰር በዚህ ጉደኛ  አንቀጽ ላይ በስደት አገር የሰበሰቡት ቅዲስ ሲኖዶስ ሕገ ወጥ ነው ይሉናል። ሊቀ ሀዋርያት (ፓትርያርክ) ቅዱስ ጴጥሮስ በሀገሩ በኢየሩሳሌም ላይ የመሰረተው ሲኖዶስ  ማገልገል ስላልቻለ እንደዛሬዋ አሜሪካ በጊዜዋ ልዕለ ሃያል በነበረችው ወደ ሮም ሄዶ በስደት ሲኖዶስ በመመምስረቱ እሱንም ህገ ወጥ ሲኖዶስ  ይሉት ይሆን?በህገ ወጥ ፓትርያርክ የሚመራውንና ወያኔ በራሱ አምሳል ጠፍጥፎ  የሰራውን ከ40% በላይ  በአንድ የትግራይ ክፍለ ሃገር ተወላጆች ጳጳስት  የታጨቀውን ሲኖዶስ «ጭቁን ሲኖዶስ» ይሉታል። ህጻን ነቢዩና ሺብሬን በጠራራ ፀሃይ የገደለው የወያኔን ሰራዊት «ጭቁን ሠራዊት» እንበለው ይሆን?በሚያሳዛዝን ሁኔታ በውጭ ያሉ ብጹዓን አባቶች ህጋዊውን ሲኖዶስ በስደተኛው ብዛትና ብሶት ተጠቅመው እንዳቋቋሙ ተናግረዋል። ባይገርሞት በስደት የሚገኘው ሲኖዶስ  ዶሮ ጫጬቶቻን በክንፋ እቅፍ አርጋ ሰብስባ እንደምትይዘው  በስደት ዓለም ያለውን ምዕመን በመሰብሰብ ሀገር ውስጥ ላለውን ተስፋ በመሆን እያገለገለ ይገኛል። በተጨማሪም በጸሎት፣በስብከታቸው እና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የሚደነቁ  የአያሌ ኦርቶዶክሳውያንን መንፈሳዊ ህይወት የለወጡ አባቶችን አቅፎ  ሀዋርያዊ ተልዕኮውን በሚገባ እይተወጣ ይገኛል። በአፍሪካ፣በአውስትራሊያ፣በአውሮፓ፣በካናዳና በተለያዩ የሰሜን አሜሪካ ግዛቶች አባቶችን በመላክ ስደተኛው ህዝብ ያጽናናልም ይባርካልም ፣በሀገር ውስጥ ህዝባችንን ላይ የሚፈጸመውን የሰብዓዊ መብት ጥሰትና የፍትህ እጦት አስመልክቶ ከስደተኛው ህዝብ ጋር ሆኖ አብሮ በመጮህ ድምጹን ወደ እግዚአብሔር ብሎም ለዓለም አብያተ ክርስቲያናትና መንግስታት  በማሳወቅ ላይ ይገኛል። ላለፉት 18 ዓመታት የደረሱበትን ፈተና በድል እየተወጣ የመጣውን በህጋዊ ፓትርያርክ የሚመራን ሲኖዶስ ሀገረ ስብከታዊ ሲኖዶስ ወይም ርክበ ካህናት ጉባኤ ተብሎ ይሰየም የሚለው መፍትሄዎም ወንዝ አያሻግርም። ህጋዊው ሲኖዶሱ ጠንክሮ ስለተገኘ ነው

ህወዓት ሽማግሌውችን እየላከ ሊደራደር የሞከረው። በወያኔ ታሪክ ከየትኛው ተቋዋሚ ፓርቲ ጋር ነው ሊደራደር የሞከረው?ይልቁንም በይበልጥ በተጠናከረ ሁኔታ እንዴት ይቀጥል የሚለው ጥያቄ ወቅታዊ ነው።

በእውነቱ ኑዛዜ የሚለው ርእስዎ አስፈላጊነቱ አልታየኝም። ምክንያቱም ሲኖዶሱ ስራውን በመቀጠሉ ፈርጀብዙ ትሩፋቶችን ለሕዝቡ አበርክቷል እንጂ ያመጣው ጉዳት የለምና። ይልቁንም ኑዛዜ ካስፈለገ ህዝብን ከዳር እስከ ዳር ያነሳሳው የቅንጅት ፓርቲ ሲከፋፈል በኢትዮጵያ የነፃነት ትግል ላይ  ቀዝቃዛ ውሃ እንደከለሰበት የታወቀ ነው።ይህንን መከፋፈል ካጧዙት መካከል የአቶ ህይሉ ሻውል ክንፍ የነበረው የሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴ  ይመሩ በነበሩት የነሻለቃ ዮሴፍ ቡድን ነው።ከነዚህ ቡድንና  ከህይሉ ሻውል ጋር የስራ  ቅርበት ወይም ደጋፊ እንደነበሩ ይታወቃል።እስቲ በኑዛዜ መልክ ያጫውቱን፤ የርስዎ አስተዋጽኦ እምን ድረስ ነበር? የሚቀጥለው ትውልድ ከዘህ ስህተት ምን ሊማር ይችላል?

ለሁለተኛ ጊዜ የጻፉት መጣጥፎ ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል ሲፈተሽ የክርስቲያናዊነት ጥያቄ ያጭራል።በመጀመሪያ በህይወት የሌለ ኢትዮጵያዊ ወንድሞን እንደኔ መልስ ሊሰጥዎት የማይችለውን መሃይም ብለው ይወርፋታል።ወንድሙን ደንቆሮ በሎ የሰደበ በቅዱስ መጽሓፋችን ምን እንደሚፈረድበት የሚናገረውን ለእርስዎ የሽቅብ ማስተማር አያስፈልግም።ግዕዝን በግሎ እንደ አንድ ቋንቋ ለመማር መጣሮ ያስከብሮታል።  አባቶቻችን ንባብ ቤት ገብተው ቅኔ ተምረው የግዕዝ ሊቅ  እንኳን ሆነው መህይም ብለው አንድን የስላሴ ህንፃ አይወርፉም ነውር ነው። ስለግል ህይወትዎ በጻፉት ላይ እንደሚነበበው ቅኔን አልተማሩም ገና መልከ ኢየሱስ ላይ ያቁሙት፤ እርስዎ እንዲሚያውቁት ግእዝን ደግሞ ከነአገባቡ  በሚገባ የሚያውቁ ሊቃውንት በቅኔ ቤት ያለፉ ናቸው፤ በመሆኑም የግል ጥረትዎ ቢያስመሰግንዎትም ያደግሞ የግእዝ ሊቅ ያሰኝዎትም፤ ሌላንም ለመተቼትም አያስችልም። እንግሊዝኛ ጠቃሽ ሁሉ እንግሊኛ አዋቂ እንዳልሆነ ግእዝ  መጥቀስም  ሊቅ አያሰኝምና።
ሁለተኛው ከብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ ጋር ስለተደረገው እርቅ፦ቅዱስ መጽሐፍ የሚያስታርቁ ብፁዓን ናችው ይለናል የሚታረቁም ብፁዓን ናችው። ታዲያ አንድን ታላቅ የኦርቶዶክስ ሊቀ ጳጳስ ይቅርታ ጠየቁ መባልን ለምንድነው እንደ ስድብ የወሰዱት?ለምን በረከትዎን በአደባባይ ያስወስዳሉ? ዋናው እኮ እርቁ መፈጸሙ ነው። እርቁ ከተፈጸመ ቤኋላ የታላቁን ኦርቶዶካሳዊ ሊቅ ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ በቀጥታ ይሁን በተዘዋዋሪ ስማችውን በመጣጥፎ ማንሳቱ አላስፈላጊ ነው። እግዝአብሔር ከመስዋዕት ብዛት፣ከእውቀት ብዛት ይልቅ የተሰበረ ልብን ይሻልና አምላካችን ለሁላችንም  የተሰበረ ልብ ይስጠን።

በመጨረሻም ወቅቱን ማገናዘብ ጠላትን ለይቶ ማወቅና እርሱ ላይ ማነጣጠር ብልህነት ነው። በዘህ ወቅት እንዲህ ዓይነት ጽሁፍ ለምን እንደሚጽፉ አልገባኝም። የመያያዋችን አጀንዳ አገራችንና ቤተክርስቲናችንን በመሳሪያ ሃይል ተቆጣጥሮ ያለውን የዲያብሎስ የግብር ልጆች ላይ  መሆኑ ቀርቶ በስደት ዓለም ብዙ መንፈሳዊ ማህበራዊና  ሀገራዊ አገልግሎት እየሰጠ ያለ አካል መሆኑ ያሳዝናል።ይልቁንም በውጭ አገር ያለውን ትግል አንድ መልክ አስይዘን በሀገር ቤት ያለውን የነጻነት ትግል እንዴት እናግዝ በሚል አጀንዳ ብንወያይ መልካም ነው። ይህም ህጋዊ ሲኖዶስን ጨምሮ የተለያዩ ሲቪክ ማህበራት፣የተለያዩ ቤተ እምነቶችና የፖሎቲካ ድርጅቶችን ጨምሮ ለሀገራችንንና ለህዝባችንን ትንሣኤ አብረው የሚሰሩበትን መንገገድ መወያያ ጊዜ ነው።አንድን ውጤታማ የሆነን ሲኖዶስ ስም ማስቀየር በምንም ዓይነት መፍትሄ አይሆንም።በተለይ ከእርስዎ ዓይነት ምሁር የሚጠበቀው ብዙ ሰው የሚቃወመውን ሃሳብ ለማንሸራሸር ሳይሆን የህዝባችንን የሰቆቃ ዘመን የሚያሳጥር ላይና የአንባቢ አዕምሮ የሚያንፅ  ቢሆን መልካም ነው። በቃላት ለመራቀቅ ጊዜው አሁን አይደለም። እርሱን ከድል መልስ እናቆየው። ድላችንን እውን የሚሆነው ያለውን እያፈረሱ ሳይሆን ባለው ላይ እየተገነባ ነው። በመሆኑም በሕጋዊ ሲኖዶስ ያልተቀፋችሁ ኦርቶዶክሳውያን  እስቲ ቆም ብላችሁ ራሳችሁን ጠይቁ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደሆነች እወቁ በእርሳም ላይ ሂዱና አንድላይ ቁሙ። በተለይ የገለልተኝነት አቋም የወሰዳችሁ ወገኖቼ ለቤተክርስቲያናችሁ ጠላት ለሆነው ሕወዓት ጥይት እያቀበላችሁ የመከራዋን ዘመን እንደምታራዝሙ አስተውሉ። ሀገር ቤት ያለው ሲኖዶስ ፓትርያርክ በህይወት እያለ ሌላ ፓትርያርክ ለመምረጥ የሚያድርገው ዝግጅት ቀኖና የጣሰ ነው። ማንም ይሁን ማን የሚመረጠው ፓትርያርክ ህገ ወጥ ነው። የሚመራውም ጉባኤ (ሲኖዶስ) ህገ ወጥ ነው።

እግዝአብሔር አገራችንን ቤተክርስቲያናችንን ይጠብቅልን

ታዬ ብርሐኑ ከቨርጅኒያ

Taye_berhanu@ymail.com